# የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት

# የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

## የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት

## የ6 ወር የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የተሰጠ

## ግብረ-መልስ

ጥር /2014ዓ.ም

## መግቢያ

የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የአሰራርና የአባላት ስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 (እንደተሻሻለው) መሠረት ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መካከል አንዱ አስፈፃሚ አካላትን መከታተል፣ መቆጣጠር እንዲሁም ድጋፍ ማድረግ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ቋሚ ኮሚቴው ከሚከታተላቸው ተቋማት ውስጥ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አንዱ ሲሆን በዚሁ መሠረት የተቋሙን የ2014 በጀት የግማሽ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በዝርዝር በመገምገም በጥንካሬ፣ በእጥረት እንዲሁም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት የሚከተለውን ግብረ መልስ ሰጥቷል፡፡

## በጥንካሬ የተለዩ ዋና ዋና ነጥቦች

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የግብይት ስርዓቱን አጭር እና ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ፤ ለውጪ ገበያ እና ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃነት የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን በመጠን እና ጥራት ለማሻሻል እና የፋይናንስ አቅርቦት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የእቃ ማከማቻ ደረሰኝ ስርዓት መመሪያ ማጸደቅ መቻሉ፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለውጪ ገበያ በሚቀርቡ የቁም እንስሳት ሀገራዊ ጥቅምን ለማስከበር እንዲቻልና በመስኩ የሚታየውን ከዋጋ በታች አሳንሶ በመሸጥ የውጭ ምንዛሬ ግኝት ማሳጣትና በመስኩ የኮንትረባንድ ንግድ እንቅስቃሴ ለመግታት የሚያስችል የቁም እንስሳት ኤክስፖርት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ መወሰኑና መመሪያ ማጸደቅ መቻሉ፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ሀገሪቷ ማንኛውም የኢኮኖሚና ማህበራዊ መስኮች ላይ መንግስት ያለው ቁርጠኝነት ለማሳየትና ከፍተኛ የሆነ ትብብር እና ቅንጅት እንዲታይበት በማድረግ መቻሉን ለማሳየት ጠንካራ የጥራት መሠረት ልማት ውጤታማና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማስቻል የብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ሰነድ ማዘጋጀት መቻሉ፣
- በወጪ ንግድ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት በተለይም ለወጪ ንግድ ምቹ የሆነ ተቋማዊ አደረጃጀት በመፍጠር፤ የምርቶችንና አገልግሎቶችን ስብጥር በማስፋት እና አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን ቁጥር በመጨመር ከወጪ ንግድ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ የኤክስፖርት ልማት ስትራቴጂ ረቂቅ ሰነድ ማዘጋጀቱ፣
- የኢንስፔክሽንና ሬጉሌሽን ሥራዎችን በማካሄድ የሸማቹንና የንግዱን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ክትትል የተደረገባቸው ፋብሪካዎች ብዛት በቁጥር በግማሽ ዓመቱ 90 ለማድረስ አቅዶ 95 በማከናወን አፈጻጸሙን 100%ማድረስ መቻሉ፣
- በሀገራችን የንግድ ሥራን ለመጀመር በአማካይ 32 ቀናት እና 11 ሂደቶችን (Procedures) ማለፍ የሚጠይቅ የነበረ ሲሆን በተሠራው የሪፎርም ሥራም በአማካይ 5 ቀናት እና 4 ሂደቶች (Procedures) ዝቅ ማድረግ መቻሉና 1,500 የነበረውን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መስጫ መደብ (ESIC) ወደ 519 እና ብቃት ሲጠየቅባቸው የነበሩ 1,350 መደቦች ወደ 10 ዝቅ ማድረግ መቻሉ፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራታቸውን፣ ደህንነታቸውንና ትክክለኛነታቸውን በመረጋገጥ በተለያዩ ዓይነት የገቢ ዕቃዎች ላይ የተደረገ የጥራት ቁጥጥር በሜትሪክ ቶን በዓመቱ 2,168,755 አቅዶ በግማሽ ዓመቱ 1,084377.55 ማከናወን ችሏል፣
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የወጪ ንግድ ገቢ ከማሳደግ አኳያ በተለያዩ ዘርፎች 1,981.19 ቢሊዮን አሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ገቢ ለማገኘት አቅዶ 1,891.3 (95%) ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ማስገኘት ችሏል፣
- በሀገር ውስጥ የሚመረቱ አስገዳጅ የሆኑ ምርቶችን በሚያመረቱ 180 ፋብሪካዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ አቅዶ በ170 (94.4%) ፋብሪካዎች ላይ የኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ ሥራ በማካሄድ ተችሏል፣

## በዕጥረት የተለዩ ዋና ዋና ጉዳዮች

- ሪፖርቱ ከእቅድና ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር በንጽጽር ሊቀርብ ሲገባው የዓመቱ እቅድ ምን ያህል እንደነበረ በማይገለጽ ሁኔታ በመቀመጡ ገምግሞ አስተያየት ለመስጠት አስቸጋሪ ከመሆኑ በላይ ሪፖርቱ የያዛቸው ቁጥሮችም ቢሆን አልፎ አልፎ እርስ በእርስ የሚጋጩና የሪፖርቱን ተዓማኒነት የሚቀንስ መሆኑ፣ ሪፖርቱ የሪፖርት ፎርማትን በተለይም ደግሞ የሪፖርት ማጠቃለያ ጭምር የሌለው መሆኑ የሪፖርት ጥራቱ ዝቅ እንዲል አድርጎታል፣
- ሪፖርቱ የክልሎችንና የተጠሪ ተቋማትን አፈፃጸም በሁሉም የትኩረት መስኮች ለይቶ አላማሳየቱ፡፡ **ለምሳሌ** የኢንስፔክሽንና የሬጉላቶሪ አፈጻጸም የሚኒስቴሩ ብቻ የያዘ እና የክልሎች አፈጻጸም የሌለ መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወደ ዘመናዊ ግብይት ስርዓት ያስገባቸው የምርት አይነቶች ብዛት ቢጠቀስም ምን ያህል መጠን አቅዶ በምን ያህል እንደ ፈጸመ አለማሳየቱ፣
- በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ከመሰራጨታቸው በፊት መመርመርና ችግር ካለባቸው ከስርጭት በፊት መታገድ ሲገባቸው በህጋዊም

ሆነ በህገወጥ መንገድ ከተሰራጩ በኋላ የቁጥጥር ስራው በመሰራቱ ከሚያስከትለው ተጽዕኖ አንጻር ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ አለመፈጸሙ፣

- የበጀት አጠቃቀም በተግባር በተለየ መልኩ አለመገለጹ እንዲሁም የኦዲት ሪፖርት ላይ የተወሰደ የእርምት እርምጃ መኖሩ አለመገለጹ፣
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያለ ምክንያት ዋጋ የሚጨምሩ ነጋዴዎች፤ የንግድ ተቋማትና ሌሎች በንግድ ዙሪያ የተሰማሩ አካላት እንቅስቃሴ ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ባለመውሰዱ ምክንያት ህብረተሰቡ ለከፍተኛ የኑሮ ውድነት መጋለጡ፣
- መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎች አቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለው ችግር ለመቅረፍ መንግስት ከቀረጥ ነጻ ማስገባት መቻሉን የሚገልጽ በሪፖርቱ የተገለጸ ቢሆንም በመሬት ላይ የሚታየውን ተጨባጭ ሁኔታና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲደርስ የህብረተሰቡን ችግር መፍታት በሚያስችል መልኩ ለመፈጸም ከክልሎች ጋር የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩ፣
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የንግድ ፖሊሲ ሥራ ዝግጅት እስካሁን ምን ደረጃ ላይ እንዳለ በሪፖርት አፈጻጸሙ መግለጽ አለመቻሉ፣
- ከተሰጡባቸው የንግድ ሥራ ፈቃድ መስኮችና አላማዎች ውጪ መነገድ ወይም መስራት፣ በኮንትሮባንድና በህገ-ወጥ ንግድ አማካኝነት ወደ ገበያ የሚገቡ የአስገዳጅ ምርቶች በየጊዜው እየጨመረ መምጣት እና ያለ ደረሰኝ ግብይት የሚከናወኑ እንዲሁም የነጋዴዎች አድራሻ በአግባቡ ተለይቶ የማይታወቅ በመሆኑ የሕብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት በተገቢው ሁኔታ ለመጠበቅ የሚያስችል ተጠያቂነት የሰፈነበት የክትትልና ቁጥጥር ስርዓትና አፈጻጸም አለመኖሩ /አለመዘርጋቱ፣
- የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥን ከማዘመን አንጻር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለክልሎች እያደረገ ያለው ክትትልና ድጋፍ አናሳ በመሆኑ የክልሎች አፈጻጸም ተቀራራቢ ደረጃ ካለመድረሱ ባሻገር በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑ፣
- ሀገራችን በተለያዩ በቁም እንስሳት፣ በጫት ምርትና በተለያዩ የቅባት እህል ምርቶች የምትታወቅበት ብትሆንም፤ በግብርና ምርቶች እና በቁም እንስሳት እየተከናወነ ባለው የህገ ወጥና የኮንትሮባንድ ንግድ ምክንያት መንግስት ማገኘት የሚገባውን ገቢ ባለማግኘቱ ይህን ለማስተካከል ህገ ወጥ የንግድ እንቅሰቃሴዎችና

ኮንትሮባንድ ንግድን ለመግታት የሚያስችል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራር አለመስፈኑ፣

- መንግስት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ዶላር ከውጭ ሀገር የሚያስገባው ነዳጅ ፍትሃዊ ስርጭት በተገቢው ሁኔታ ካለማከናወኑ በላይ የነዳጅን ምርት ኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ ለመግታት የሚያስችል ጠንካራ አሰራር አለመዘርጋቱ፣
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት ማዘገየትና በፍተሻ ውጤት ሪፖርት ላይ ከደንበኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለመፍታት የሚመለከታቸውን የስራ ተቋም የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ባስወገደ መልኩ እና ቀልጣፋ ስራ እንዲሰራ አለማድረጉ፣

## የትኩረት አቅጣጫዎች

- በሪፖርት የተገለጹ አፈጻጸሞች ከሂደት ይልቅ ውጤታቸውና ያስገኙት የህዝብ ጠቀሜታ ላይ ትኩረት ተደርጎ መገለጽ አለበት፣
- ህግ ወጥ ንግድ  በሀገር ኢኮኖሚ ላይ እና በህዝብ ህይወት ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ በቀላሉ የሚካካስ ወይም የሚመለስ ባለመሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በክትትልና ቁጥጥሩ ላይ የሚሳተፉ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ከብልሹ አሰራርና ከሙስና የጸዱ ለማድረግና በንግዱ ላይም የሚሳተፉትን የንግዱ ማህበረሰብ ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ አሰራር መዘርጋት አለበት፣
- የነዳጅ ስርጭት በተለይም የኮንትሮባንድ ስጋት ባለባቸው ቦታዎች ላይ ከመጀመሪያ ከሚሰራጨው የነዳጅ መጠን መወሰን ጀምሮ ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፣
- የፍጆታ እቃዎች አቅርቦት ላይ የረጅም ጊዜ አማራጭ አሰራር ከማቅረብ በተጨማሪ በአሁኑ ሰዓት ሀገሪቱ ያላትን የውጭ ምንዛሪ አማራጮችን ያዋለችበት ጉዳይ በመሆኑ የስርጭቱ ፍታሃዊነት፣ ወቅታዊነት እና ተደራሽነት እንዲረጋገጥና በአግባቡ እንዲሰራጭ በልዩ ትኩረት መሰራት አለበት፣
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰሩ የህግ ማዕቀፎች ተጠናቀ ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ ይኖርበታል፣

- ሀገራችን ከአጎዋ (AGOA) የገበያ እድል ተጠቃሚነት እንድትሰረዝ መደረጉ የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን እድል የሚተኩ ሌሎች አማራጭ ገበያዎችን የመለየት ስራ ልዩ ትኩረት ተደርጎበት መስራት ይኖርበታል፣

- ሀገራችን ወደ ውጭ በምትልካቸው እንዲሁም ከውጭ በሚገቡ እቃዎች የሚፈጸም ህገ ወጥና የኮንትሮባንድ የንግድ እንቅስቃሴ ለመግታት የሚያስችል እና ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎችም ሆነ ከውጭ ገብተው ለሀገር ውስጥ ተጠቃሚ የሚሰራጭ እቃዎች ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ለማስቻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጠበቀ ቅንጅታዊ አሰራር በመመስረት የተጠናከረ ስራ ሊሰራ ይገባል፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሳለጠ ሀገራዊ የገበያ ማዕከላት (የቅዳሜና እሁድ ገበያ) ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመነጋገር በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በስፋት በመገንባት አምራቹ ከተጠቃሚውን ህብረተሰብ ጋር በቀጥታ የሚገናኝበት ሁኔታ በመፍጠር የምርት አቅርቦትና ስርጭት እንዲሻሻል፣ የዋጋ ንረት እንዲስተካከል፣ እንዲሁም አምራቹ ምርቱን የማያስተዋወቅበትን ስራዎችን በአግባቡ መስራት የሚያስችል አሰራር ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፣

- ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ከአደረጃጀት ጀምሮ ለቀጠናዊ ትስስር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይኖርበታል፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የውጭ ገበያን ከማፈላለግ አንጻር ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ላይ ቁጥጥር ከማድረግ ባሻገር በማምረት ሂደት ውስጥ የሚከሰቱ የምርት ጥራት ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ዘርግቶ መስራት ይኖርበታል፣

- የማኑፋክቸሪንግ ተቋማት የማምረት አቅማቸውን የማሳደግና የግብይት አቅርቦት ችግሮችን የሚቀርፉበት አሰራር በመዘርጋትና ከግብይት አቅራቢ ተቋማት ጋር በመደጋገፍና ከችግሩ በማላቀቅ አምራችነታቸውን በማሳደግ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲወጡ ከፍተኛ ትኩረትና ድጋፍ ተደርጎበት መሰራት ይኖርበታል፣

- ሀገራችን የአለም ንግድ አባል ለመሆን የምታደረገውን ሂደት ለዓለም ንግድ ድርጅት ድርድር በግብዓትነት የሚሆኑ እንድምታ ጥናቶችና የድርድር ሰነዶችን የማዘጋጀት ስራዎችን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት አለበት፣

- በንግድ ስርዓቱ ዙሪያ እየተከሰቱ ያሉ ህገ ወጥ አሰራሮችን ከመታገል አንጻር የክትትልና ቁጥጥር ስራውን ተጠያቂነትን ባረጋገጠና ዘለቀታዊ ችግር ፈቺ የሆነ አሰራር መዘርጋት አለበት፣

- ቁጥጥር በሚደረግባቸው አስገዳጅ ምርቶች፤ አምራችና አቅራቢዎች ላይ የሚወሰዱ የክትትል እርምጃዎች ለዘብተኝነትና ቸለትኝነት የሚታይባቸው መሆኑን ከሪፖርቱ መረዳት ይቻላል፡፡ (ለምሳሌ፡- ምርቱን አላስመረምርም ያለን በማስጠንቀቂያ ማለፍ፤ ድርጅቶች ከተዘጉ በኋላ በቀላል ማስተካከያ መክፈት) የታዩ በመሆኑ ሂደቱ በማህበረሰብ ህይዎት ላይ ከሚያስከትለው ቀውስ አንጻር መስተካከል ያለበትና ልዩ ትኩረት የሚሰጠውና የሚወሰደው የእርምት እርምጃ ተጠያቂነትን ያረጋገጠ ሊሆን ይገባል፣

- አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ወደ ታችኛው የአስተዳደር እርከን በማውረድ ለሕዝብ ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር ስርዓት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶበት መስራት ይኖርበታል፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ማለትም ለሴቶች፣ ኤች አይቪ ኤድስ ተጽዕኖ ለመከላከል፣ አካባቢ ጥበቃ፣ አካል ጉዳተኞችና ወ.ዘ.ተ ጉዳዮችን ትኩረት አደርጎ መስራት አለበት፣

- የንግድና ዘርፍ ማህበራት እንደ ብዛታቸውና በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ እንዳላቸው ተሳትፎ በበቂ ሁኔታ እንዲደራጁና የተጠናከረ ስራ እንዲሰሩ ኃላፊነት የተሞላበት አገልግሎት እንዲሰጡ የሚደረግላቸው ድጋፍና ክትትል ተጠናክሮ መሰራት አለበት፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችና የቁም እንስሳት ወደ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት እንዲገቡ ማዕከላትንና መሠረት ልማትን በሁሉም ክልሎች በበቂ ሁኔታ ማስፋፋት ትኩረት ተደርጎ ሊሰራ ይገባል፣

## ማጠቃለያ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ 2014 ዓ.ም የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀምን በዋና ዋና ተግባራትና ግቦች ላይ ያከናወናቸውን አፈፃፀሞች በመመልከት በጥንካሬ፣ በዕጥረት እና ለቀጣይ ትኩረት የሚሹትን በመለየት በዚህ ግብረ-መልስ የላክንላችሁ ሲሆን መ/ቤቱ በስሩ ያሉትን ተጠሪ ተቋማት በመደገፍና በማጠናከር የተቀናጀ ውጤት እንዲያመጣና የአገራችንን ሕዝቦች ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ሥራ በመስራት የተግባራት አፈጻጸም እንዲሻሻል እንዲሁም የሁሉንም ተጠሪ ተቋማት አፈጻጸም በቂ ክትትል እንዲደረግበት ቋሚ ኮሚቴው ያሳስባል፡፡

**ከንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ**